homes victoria

50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

**OFFICIAL**

ነዋሪ
200 ዶርካስ ስትሪት
ሳውዝ ሜልበርን

ውድ ነዋሪ

ስለ ሆምስ ቪክቶሪያ ታልቁ የቤቶች ግንባታ (Big Housing Build) እድገት እና ስለ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ማልማት መርሃ ግብር ያለው አዲስ መረጃ ለማሳወቅ እየጻፍንልዎት ነው።

አሁን ፣ የሚቀጥለው ደረጃ በ 7 አዳዲስ ቦታዎች በመካሄድ ላይ ነው። ይህ ማለት በ9 ሰፈሮች ወይ ሳበርቦች ለሚኖሩ የአሁኑ እና የወደፊት ነዋሪዎች የተሻሉ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ የሆኑ ቤቶች ወደ ማቅረቡ እያመራን ነው። **የዛሬው ማስታወቂያ በቤትዎ ወይም በሕንጻዎ ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።**

## ዛሬ ይፋ የተደረገው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና ስለማልማት ከነዋሪዎች ጋር ተነጋግረናል፡-

- 25 እና 27 ኪንግ ስትሪት፣ ፕራሃን
- 150 ኢንከርማን ስትሪት፣ ሴይንት ኪልዳ
- 150 ቪክቶሪያ አቬኑ፣ አልበርት ፓርክ
- 159 ሜልሮዝ ስትሪት፣ ኖርዝ ሜልበርን
- 29 ክራውን ስትሪት፣ ፍሌሚንግተን
- 94 ኦርመንድ ስትሪት፣ ኬንሲንግተን

**ከጁላይ 2026 እስከ ፌብሩዋሪ 2028**፣ ብዙ እና የተሻሉ ቤቶችን በምናቀርብበት ጊዜ ወደ ተስማሚ ቤት እንዲዛወሩ ለመርዳት በእነዚህ ቤተሰቦች ውስጥ ከሚኖሩ ነዋሪዎች ጋር በቅርበት መስራት እንጀምራለን።

## በአቅራቢያዎ አዳዲስ ቤቶችን እየገነባን ነው

እነዚህን ነዋሪዎች የመዛወሪያ አማራጮችን ለመደገፍ አዳዲስ ቤቶች በአቅራቢያው በመሰራት ላይ ናቸው። በዚህ አመት ሊጠናቀቁ ነው እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ኤሴክስ ስትሪት፣ ፕራሃን
- ሲሞንስ ስትሪት፣ ሳውዝ ያራ
- ባራክ ቢኮን፣ ፖርት ሜልበርን
- ሆላንድ ኮርት፣ ፍሌሚንግተን

እነዚህ ቤቶች ለማሞቅ እና ለማቀዝቀዝ ቀላል ይሆናሉ፣ የመንቀሳቀስ እክል ላላቸው ሰዎች የበለጠ ምቹ ይሆናሉ እንዲሁም የህዝብ ማመላለሻ በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም በነዚህ ቤቶች ደህንነትን፣ ብርሃንን እና አየር ማናፈሻን ተሻሽሏል እንዲሁም በረንዳዎች እና የግል የልብስ ማጠቢያዎች አብረው ይኖራሉ።

## በሰፈራችሁ

የእርስዎ ሕንፃ የሚቀጥለው የመልሶ ማልማት ደረጃ አካል አይደለም። ከጃንዋሪ 2028 በፊት ምንም ተጨማሪ ማዛወር አይከሰትም፣ እና ጊዜው ሲደርስ ከእርስዎ ጋር እንገናኛለን።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአካባቢያችሁ፣ የኮመንዌልዝ እና የቪክቶሪያ መንግስታት 131 አዳዲስ ማህበራዊ ቤቶችን ለማቅረብ በታላቁ የቤቶች ግንባታ እና ሃውሲንግ አውስትራሊያ ፍዩቸር ፈንድ (Housing Australia Future Fund) በኩል በጋራ እየሰሩ ነው። ይህ የሳውዝ ሜልበርን አከባቢን ለማደስ የመጀመሪያው እርምጃ ሲሆን ራዕዩ ጥራት ያላቸው ቤቶች፣ ደህንነቱ በተጠበቀ፣ በጥሩ ሁኔታ በተነደፈ እና በደንብ በተገናኘ ሰፈር ውስጥ ማቅረብ ነው።

## በሌሎች ቦታዎች ምን እየሆነ ነው?

በ**ካርልተን በሚገኘው የኤልጊን እና ኒኮልሰን ስትሪቶች**፣ የአዳዲስ ቤቶች ዕቅዶች በነዋሪዎች ግብአት ይመራሉ። 248 አዳዲስ ቤቶችን በ2028 ለማድረስ የማፍረስ ስራ በመካሄድ ላይ ነው።

በ**ፍሌሚንግተን እና በኖርዝ ሜልበርን ማዛወር እየተጠናቀቀ ነው።** ማፍረስ ለመጀመር እየተዘጋጀን ነው እና ቀጣዩ ደረጃ ለአዳዲስ ቤቶች እና የማህበረሰብ መገልገያዎች ዲዛይኖች ላይ ነዋሪዎችን አስተያየት እንዲሰጡ መጋበዝ ይሆናል።

በ**ሳውዝ ያራ እና ሪችመንድ** የሚገኙ ብዙ ቤተሰቦች በአቅራቢያው ወደሚገኙ አዳዲስ ቤቶች ተዛውረዋል። ከ85% በላይ የሚሆኑ አባወራዎች ተዛውረዋል፣ ወይም በመዛወር ላይ ናቸው፣ እና ሁሉም እስከ የካቲት 2026 ለመዛወር በሂደት ላይ ናቸው።

## ወቅታዊ መረጃ ያግኙ፣ ከኛ ጋር መገናኘትዎም አያቋርጡ

በቋንቋዎ ጨምሮ ስለ መልሶ ማልማት ሂደት መረጃ ለማግኘት homes.vic.gov.au መጎብኘት ይችላሉ። መደበኛ ወቅታዊ እና አዲስ መረጃዎች ለማግኘት በመመዝገብ ከእኛ ጋር መገናኘትዎን መቀጠል ይችላሉ።

ከሰላምታ ጋር

**Simon Newport**
ዋና ሥራ አስፈፃሚ
ሆምስ ቪክቶሪያ

28/01/2026